የመቐለ ዩኒቨርሲቲ

የሕግ-ተማሪዎች ድምፅ


FREE THINKING FOR BETTER FUTURE



ቁጥር. 2



ሰኔ 2009 በየሁለት ወሩ የሚታተም



የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች ድምፅ

"የሕግ ተማሪዎች ድምፅ" *(MULSSA VOICE) ሰኔ 2009 ጀምሮ በየ ሁለት ወሩ የሚታተም በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የሕግ ትምህርት ቤት መፅሔት ነው፡፡ መፅሔቱ ከማንኛውም ብሔር፣ ኃይማኖት እና የፖለቲካ ድርጅቶች አስተሳሰብ ጋር ያለወገነ የሕግ ተማሪዎች ነፃ ሓሳብን የሚያስተናብር ነው፡፡*

የአዘጋጁ መልዕክት፡- እስኪእንወቃቀስ፡ እንዲህ ቢሆንስ ይወዱታል እና ሌሎችምን ስራዎች ከመልሳ .....መልካም ክረምት ለሁላችን ፤፤

- ዋና አዘጋጅ ሚኪያስ መላክ ብርሀኔ
- አዘጋጆች አብዱረሕማን ሻሎ ዘላለም አበራ ማርቆስ ጌታቸው
- ዋና ኤዲተር አንተነህ ዘሪሁን
- ሥርጭትና ተዛማጅ ክንውኖች ሐቤክ ሥዩም በህቨን ሐ. አሳታሚ የመቐለ የኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት የሕግ ተማሪዎች ማሕበር መልሳ

ማውጫ

- ሰሞንኛ ወሬ (ዜና የዓዲ ሓቂ ተማሪ ህብረት @ በተወልደ
- እስቲ እንወቃቀስ "እንዲቢሆንስ? ዘመቻ ቫንዳል Students..." በዘላለም አ.
- መልሳ በ2009 ዓ.ም የብዙ ስራዎች እና ክስተቶች ባለቤት ሁኗል፡፡ገፅ 3
- ወቅታዊ ጉዳይ "...ካምናው ካልተማርን ..." በቃለአብ ይ...--ገፅ 4
- የፋይፀፅ ራዕይ ቁጥር-1 ምዕራፍ አንድ አስማተኛዋ መንደር @በፍፁም አብርሀም....ገፅ 5
- የሕግ ጉዳይ" በጦርነትም ህግ አለ ...የጠፋ እቃ አግኝተው ያውቃሉ?" በህቨን ሐ. ----ገፅ 7
- የጨንቻው ሊቅ ©በብሩክ ተስፋዬ.....ገፅ 8
- ኪነ-ጨዋታ"ላንዴ...!...ንባባችን" በአንተነህ ዘ. 8
- የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ዶክተር ክንደያ ገብረሂዎት የተገኙበት የመልሳ የአመቱ የፍፃሜ ታላቅ መሰናዶ

ምስጋና

ይህን የመልሳ ቮይስ መፅሔት በማዘጋጀት ጉልህ ሚና ለነበራቸው ለሁሉም ለመልሳ ቮይስ መፅሔት አዘጋጅ(ኤድቴሪያል) ኮሚቴ እንዲሁም ለመፅሔቱን እውን መሆን በተለያየ መልኩ ላገዙን እና ላበረታታቱ ሁሉ በመልሳ ቮይስ መፅሔት አዘጋጆች ስም ላመሰግን እወዳለሁ::

ማሳሰቢያ፤ ይህ ቦታ ለስፖንሰር ክፍት ነው ምርትዎን እና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ::

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች ድምፅ

“የሕግ ተማሪዎች ድምፅ” (MULSSA VOICE) በ2009 ዓ.ም ጀምሮ በየ ሁለት ወሩ የሚታተም በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የሕግ ትምህርት ቤት መፅሔት ነው:: መፅሔቱ ከማንኛውም ብሔር፣ ኃይማኖት እና የፖለቲካ ድርጅቶች አስተሳሰብ ጋር ያልወገነ የሕግ ተማሪዎች ነፃ ሓሳብን የሚያስተናብር ነው::

Mail address
mikiasmelak@gmail.com
Phone No: 09 20 66 65 95

Mail address
mikiasmelak@gmail.com
Phone No: 09 20 66 65 95

ከሰሞኑ...

የዓዲ ሓቂ ተማሪ ህብረት

@ተወልደ ገ/መድህን

ዕለት 3/10/09 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ለቀጣይ ዓመት ማለትም 2010 ግቢውን በተማሪ ህብረትነት የሚያገለግሉ ተማሪዎች ለመምረጥ ዓላማ ያደረገ ስብሰባ ተካሂዷል፡፡ በዕለቱም ተማሪዎች ከሊስት ስማቸው እየተነበበና አባልነታቸው እየተረጋገጠ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በዕለቱም ከተለያዩ ፅ/ቤቶች እንግዶች የነበሩ ሲሆን የድህነት ዳይሬክተር፣ የዓዲ ሓቂ ግቢ ተማሪዎች አገልግሎት አስተባባሪ፣ የዓይደር ተማሪዎች ህብረት ፕረዚደንት፣ የሰላም ፎረም፣ የተማሪዎች ፖሊስና የሰርዶ ጥበቃ ተወካዮችን በታዛቢነት ያካተተ ነበር፡፡

መድረኩም በዓዲሓቂ ግቢ ተ/ህ አስተባባሪ ተማሪ አድነን እየተመራ የተጀመረ ሲሆን ሂደቱም በተለያየ ምዕራፍ ነበሩት፡፡ በመጀመርያ እንግዶች ሃሳባቸው እንዲገልፁ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች /ፓርላማ አባላት/ ሂደቱንም ምን መምሰል እንዳለበት ሃሳብ እንዲሰጡ ከተደረገ በኋላ ለቀጣይ ዓመት ለሚቆዩት ተማሪ ህብረትም በህጉ መሰረት የህብረት የሰጣቸው ግምገማ ከተነበበ በኋላ የፓርላማ አባላቱም ህብረቱ በተማሪ ህብረቶቹ ከነሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን በተጨማሪ የራሳቸው ሃሳብ በ3ቱ ተማሪ ህብረቶች አስተያየታቸው ሰጥቷል፡፡

በአጠቃላይ ምርጫው ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ፣ ከዓምና የበለጠ ፍትሃዊነትና ማመዛዘን የታየበት ተወዳዳሪዎችም በስራቸውና በአቅማቸው መሰረት ድምፅ የተሰጡበትና ፓርላማ ልክ እንደ ዳኛ ሆኖ ፍርድ የሰጠበት ነበር፡፡

በመጨረሻም ፓርላማው ተማሪ ክንፉ ገ/ዮሃንስን በአብላጫ ድምጽ የተመረጠ ሲሆን ተማሪ ሠመረም በሁለተኛነት አሸንፉዋል፡፡ ይህ ማለት ደሞ ተማሪ ክንፉ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተወካይ እንዲሁም ተማሪ ሰመረ የዓዲ ሓቂ ግቢ አስተባባሪ ሁነው ተመርጧል ማለት ነው፡፡



የ3ኛ አመት የህግ ተማሪዎች በባህር ዳር ከተማ ጣና ላይ የጀልባ ጉዞን የሚያሳይ



የ2009 ዓ.ም የመልሳ አመራሮች



ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ መልሳ ከባህርዳር የህግ ተማሪዎች ህብረት እና የህግ ት/ቤት ሀላፊ ከስብሰባ በኋላ

የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

እንዲ ቢሆንስ?

© በዘላለም አበራ

ሠላም ለናንተ ይሁን ወዳጆቼ! እንዴት አላችሁ? መቼስ ይህቺ ሰላም ምትባል ነገር ትርጉሟም ምግባሯም ሲጥም፣ ግና ምን ያደርጋል እንደው በቀላሉ አትገኝም ብዙ ታለፋለች ማስናፈቅ ትወዳለች ስትገኝ ግን ማለፍያ ነው ፍሬውን የጠበቀ በለሱን ይበላል አይደል ሚለው መፅሀፉ፡፡ ብዙ ገተታ አላብዛባችሁ እና ዛሬም እንወቃቀስ እና እንለወጥ፣ እንስተካከል የማንበብ ባህላችን እና ለትምህርት ምንሰጠው ቦታ ትንሽ ተጣሟል ለማለት ነው የተከሰትኩት፡፡

የሰው ልጅ አካባቢውን አውቆ በተፈጥሮ ላይ ለመጎልበት ኑሮውን በቀላል መንገድ ለመምራት ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አዲስ አሳብን አግኝቶ ተፈጥሮን አመቻችቶ ወይም ራሱን ከተፈጥሮ ጋር አስማምቶ ለመኖር ባለው ፅኑ ፍላጎት አካባቢውን በጥሞና ያጤናል። ችግር ሲገጥመውና አውቀት ሲያንሰው ከሌሎች ጋር ለመነጋገር ለመወያየት እንዲሁም በማንበብ መፍትሄ ለመሻት ይጥራል። ለችግሩ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ በሚሏቸው ነገሮች ዙሪያ መላምቶችን ይደረድራል እሙኖችን እና ቲዎሪዎችን ይቀምራል። ለነዚህም ማረጋገጫ ሊሆነው የሚችል መረጃ ይሰበስባል፣ ይመረምራል፣ ይተረጉማል። በመጨረሻም መላምቶችንና ቲዎሪዎችን ካገኛቸው መረጃዎች አንፃር ተቀባይነታቸውን ይፈትሽና ወደ መደምደሚያ ይደርሳል። ይህንንም በሥርዐት /በተቋም/ እና በካሪኩለም ቀርፆ ለትውልድ ያሸጋግራል። ተቀባይውም ትውልድ በምርምር እየታገዘ እየጨመረ፣ እያሻሻለና እየቀነሰ

ስለነበርና ስለሆነ ብዙ መሻሻል ያለባቸው አስተሳሰቦችና አኗኗሮች እንዳትቋም የቀረው እድገታችን እና በስጋት ላይ ያለው ያገራችን ቀጣይነት መስካሪ ናቸው። ለዚህም ይህን ኃላፊነት ከድሮቹ እኛ መቀበል እንዳለብን ማህበረሰብም ምን ያህል መፍትሄ ጠቋሚና dynamic የሆነ ተሜ እንደሚፈልግ ከአንድም ሶስት አራት ማሳያ መጥቀስ ይቻላል። እኛ ዘመኑ የኛ እንደሆነ ማሳየቱ ተስኖናል። አንዳንዱ ተሜማ ቱሪስት ነው ሚመስለው። ምን እንደሚማር እንኳ በቅጡ የሚያውቅ አይመስልም። ለትምህርቱ ሚሆን ትንሽ ጊዜ እንኳ መለገስ ፈቃደኛ አይደለም። ነገሮችን ምን፣ ለምን እና እንዴት ማረግ እንዳለበት ግራ ተጋብቷል አላማና ግብ ያው አይመስለም። ሌሎች መፃፍችን እያነበበ እያስተዋለና እየመረመረ እራሱን ባለ ማብቃቱና ባለመዳበሩ ትምህርቱን እየተዝናና እና እንደፈለገው እየሆነ መማር ማወቅ እንደሚችል ማገናዘብ የተሳነው ይመስለኛል ሁላችንም ብዙ ፍላጎቶች አሉን...ይዞብን የመጣው ብዙ ችግሮች አሉ የሰው አይምሮ ባለጌ ነው ካልያዝነው ደርዝ ካላበጀንለት ገደል ይዞን ይገባል ምድር ላይ እስካለን ድረስ ጊዜና ሁኔታ ሚገድቡን ይመስለኛል ሁሉም ነገር ደሞ ፍላጎትና መብት ብቻ ሳይሆን ጥረት እና ግዴታ ይዞብን ይመጣል። ማህበረሰቡ እንዴት እና በምን ሁኔታ ዛሬ ድረስ እኔ እንዴት መሆን አለብኝ ሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ማንበብ፣ መማርና ማወቅ የሚፈልጉ ናቸው ብዬ አስባለው። እኛ ግን ይህን ባለመገንዘባችን አጠባባችን ሚከሰቱ ለውጦችን ማወቅና አብሮ መሄድ ተስኖናል። ተሜው ውጤታማ ካልሆነ ሀገር ሁሌም የድርቅ፣ የራሀብ እና የወረርሽኝ መጫወቻ እንደምትሆን ሁል ጊዜ ከሰው ጠባቂ /ከአስተማሪ/ በማንኪያ አጉርሱኝ ባዮች ሆነናል። የምንፈልገው ለመመረቅ ብቻ ነው ሚመስለው የትምህርት ጠቀሜታ ምንነት ካለመረዳታችን የተነሳ ነጥብ ለማምጣት ብቻ ነው ትምህርቶችን ምናነበው። ትምህርቱን አስተማሪውና ሀንዳውት ካለን እና...ውጭ ማንበብና መመርመር እንዳብን አልተረዳንም። ሊያውም ዘመኑ ረቆ እንደፈለግነውን እውቀትና መፅሀፍ ከመረጃ መረብ ማግኘት እያቻልን ከትምህርታችን ውጪማ ያሉ መፃህፍቶቼን ማንበብ አይደለም ሌሎች አንብበው ሲወያዩ እንኳ መስማት ያንገሸግሸን ጀምሯል። ጉድ እኮ ነው! ይመስለኛል አሁን ምንማራቸው ትምህርቶች ተፈጥሮን ለማወቅ፣ ለኑሮአችን አመች ሁኔታን ለመፍጠር፣ ተፈጥሮ ላይ በተቻለን ደረጃ ለመጎልትና ከጊዜው ጋር ለመራመድ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። ምንማራቸው ወደ ተግባር ቀይረን ስንጠቀማቸው አይስተዋልም። ለዚህም ምክንያቱ ልክ እንደፈረሰ ነገሮችን ባንድ አቅጣጫ እንደናረግ ያረገው የሞተ የንባብ ባህላችን እና ለሳይንስ ምንሰጠው የተጣመመ ግምት ናቸው ብዮ አስባለሁ። አስቡት አንድ ተሜ እዚህ ግቢ ለ3 እና 5 ዓመታት ተምሮ ከማህበረሰቡ ጋር ሲቀላቀል የተሻለ አስተሳሰብና እውቀት ከሌለው ምኑ ላይ ነው ተማረ ሚባለው? ሊያውም ያልተማረ ዜጋ እንደ እንደአሻን የፈለጉት አገር ላይ ለውጥ እና እድገት "ሀራም" እየሆነብን እኮ ነው። አንድ ዶናልድ ሌፊው የተባለ የውጭ ፀሀፊ "አፍሪካን ወዳታለሁ፣ ምክንያቱም ድሮን ታስታውሰኛለች" ብሎ ተሳልቆብናል። የማህበረሰብ እድገት ማምጣት እየተሳነን ነው። ማህበረሰባችን እንደሆነ ጠቃሚ ትምህርትና አስተሳሰቡ ቢያስተምረንም አሉ ገና በሳይንስና በምርምር ያልዳበረ ይቀጥላል ይህን ሂደት ስናስተውል ምርምር የሰው ልጅ የሕይወት /ኑሮ/ አካል መሆኑን እንረዳለን። ለዚህም ይመስለኛል ትምህርት የለውጥ እና የእድገት መሰረት እንደሆነ ሁላችንም የምንስማማበት፡፡ ብዙ ምሁራንም ትምህርት ለአንድ ማህበረሰብ እድገትና ቀጣይነት የአንበሳውን ሚና እንደሚጫወት ብዙ ትንታኔ ሰጥተውበታል። ከነዚህም መካከል ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሙሁር ገ/ህይወት ባይከዳኝ ተጠቃሽ ነው። ታድያ ሀገረ መንግስታትም ይህን ለማሳካት ጠንካራ የትምህርት ተቋም እና ደምበኛ የትምህርት ፖሊሲ ማዋቀርና ማርቀቅ ቀዳሚ እና መደበኛ ተግባራቸው እንደሆነ ጠለቅ ያ ትንታኔ ሰጥቶበታል። በዚህ መሰረት ሄደው የአገራቸውን እድገትና ቀጣይነት ያረጋገጡ አያሌ አገረ መንግስታት እንዳሉ ግልፅ ነው ለትምህርት ተቋሙ እና በሙሁራኑ ነፃነትን በመስጠታቸው፣ ለምርምር ትልቅ ቦታ ሰጥተው አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላታቸው ዛሬ ላይ ከምድር አልፈው የጠፈር አካላትንና ምንነትን ለማወቅ በቅተዋል። ከነርሱ አልፈው የኛ ባህል፣ አስተሳሰብና አኗኗር ላይ ሳንወድ በግዳችን ጫና እያሳደሩ ነው። ግና ምን ያደርጋል ምስኪኑና ደሀው የአፍሪካ ሕዝብ ለዚህ አይነቱ ሁኔታ የታደለ አይመስልም። ለዚህም ምክንያቱ አምባገነን አገረ መንግስታት መብዛት፣ የትምህርት ፖሊሲውም ሆነ ተቋሙ ደካማ መሆን ተጠቃሽ ቢሆኑም ከዘመናችን አንፃር የተጫው ድርሻ የላላ ይመስለኛል በዚህ በቅርብ ከምንመለከተው ከጊቢያችን እንኳ አብዛኞቻችን ተሜዎች ለለውጥ፣ ለምርምር ለንባብ ምንሰጠው ግምትና ቦታ እዚህ ግባ እሚባል አይነት አይደለም

ያለንበት ሃገራዊ ሁኔታ ያሳያል። ተሜው ግራ ስለገባው አንዳንድ አስተማሪውም ከሱ ያልተሻለ እንደውም ከተሜው የባሰ በመሆኑ የትምህርት ጠቀሜታና ትርጉም ባልተማረው ሆኗል፡፡ የሚሰጥና yሚተነትነው ማን ነበረ በናታቹ... የተገላቢጦሽ አህያ ወደ ቤት ውሻ ወደ ግጦሽ ብሎ የገጠመው። ማህበረሰብ ያቋቋማቸው ተቋማት (institution) እርስ በእርስ የተሳሰሩ (interrelate) በመሆናቸው በተለይ የትምህርት ተቋሙ የትምህርት ተቋሙ የፈረሰ እና አቅም ያጣ ሲሆን ማህበራዊ እድገቱ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ግብረገባዊነት እንደሚያሽቆለቁሉ እርዳታ ባህሪው የሆነውን የአፍሪካ ህዝብ ማየቱ ከበቂ በላይ ነው። አንድነት፣ መከባበር፣ መደጋገፍ፣ የአብሮ መኖራችን ዋስትና መሆናቸውን ሊለየን አልቻለም። ተፈጥሮአችን የሆነውን ምክንያታዊነት በስሜታዊነት የገደበንን ነው ሚመስለው። አንድ አፍሪካ ተብለን ከተመሰረትን ስንት አመታት ነገዱ እኛ ግን ባለፈው በማይጠቅም ነገር እየተነታረክን ዛሬን ረስተን 55ተኛ አገር መስርተናል ገና 100 የማረግ እቅድ ነው የተያያዝነው። ሀይማኖት፣ ዘር፣ ባህል፣ ኢኮኖሚና ሳይንስ ምን እና እንዴት መሆን አለባቸው ለአንድ ማህበረሰብ እድገትን ማምጣት እያቃተን ነው። ቆም ብለን ችግራችንን እንፈትሽ እንጂ። ችግራችንን በሚገባ በመማር፣ በማንበብና በማስተዋል መፍትሄ ለመስጠት እንችላለን። እኛ ተሜዎች የራሳችንን ዕዕዕ በራሳችን ካስወገድን የሌላውን ማንዛት አይከብደንም። አውቀንና ተመራምረን ተደጋግፈን ከተጠበብንባት ምድር ለሌላ የሰጠችውን ለኛ ምትነሳበት ነገር አይታየኝም። የዛሬ ትንሽ ለውጥ ለህይወታችንና ለኑሮአችን ሰናይ መሆን አንድ እርምጃ ነው እያልኩ በዚህ ጥቅስ ሀሳቤን ቋጫለሁ፡፡

“You never wrong to do the right thing”

ቸር እንሰንብት!

Justice for all



3rd year half-life at Bahirdar

MEKELLE university law school student’s association (MULSSA)

መልሳ በ2009 ዓ.ም የብዙ ስራዎች እና ክስተቶች ባለቤት ሁኗል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ የመልሳ አመራሮች የተለያዩ ስብሰባዎችን እና ፕሮግራሞችን በማስተባበር የጀርባ አጥንት ሁነዋል፡፡ አዎ! ከዚያም አልፎ አብሮ ከመስራት ባሻገር ባይነቱ የተለየ 9 የመልሳ አመራሮችን እና 5 የዳጀስት አባላት የያዘ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ወደ ባህርዳር እና ጎንደር በመሄድ የኢትዮጵያ ህግ ተማሪዎች ህብረት ለማቋቋም ከሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ታሪካዊ የሆነ የሁለትእዮሽ ስምምነት ሰነድ በመፈራረም በድል ተመልሷል፡፡

የመልሳ ካፕ የእግር ኳስ ጫዋታን ለህግ ተማሪዎች ብቻ በማዘጋጀት እንደመጀመሪያነቱ ብዙ መስተካከል ያለባቸው ነገሮች ቢኖሩም በስኬት በማጠናቀቅ ሴክሽን ሁለት አንደኛ የወጡት ፍሬሽ የህግ ተማሪዎችን የዋንጫ ባለቤት አድርጓል የ1200 (አንድ ሽህ ሁለት መቶ ብር) አግኝተዋል፡፡ ሁለተኛ የወጡት ሴክሽን ሁለት የአራተኛ አመት የህግ ተማሪዎች የ500 መቶ ብር አግኝተዋል፡፡ ለጥሎ ማለፍ አራቱ ውስጥ ለገቡት ሴክሽን ሁለት ስምስተኛ አመት የህግ ተማሪወች እና ሴክሽን ስምስት አራተኛ አመት ሰርተፍኬት አበርክቷል፡፡

ለስምስተኛ አመት የህግ ተማሪዎች half-life (የሁለት አመት ከግማሽ ቆይታን) ምክንያት በማድረግ ታይቶ በማይታወቅ ልዩ ሁኔታ ባህር ዳርሂደው አንዲያከብሩ አድርጓል፡፡ ፕሮግራማቸውም ልዩ እንደነበረ እና ጣና ሐይቅ ላይ አባቸኮል ደሴት ውስጥ በፓሪ እንደተከበረ እና መቸም የማይረሳ ልዩ ጊዜ እንዳሳለፉ ተናግረዋል፡፡

በህግ ት/ቤት በሴክሬት ባሎት በተደረገ የሞዴል መምህር እና ተማሪዎች ምርጫ ሁሉም ህግ መምህራን እና ተማሪዎች ተመራጭ እፁዙ የነበሩ ሲሆን ባገኙት አብላጫ ድምፅ እውቅና አግኝተዋል

በ2009 በጥሩ አርዓያነት (ሞዴልነት) የተሸለሙ ሞዴል መምህራን

1. **ገብረአብዝጊ ወልደስላሴ**
2. **ሀሰን ሞሀመድ**
3. **ካሓሳይ ደበሱ**
4. **ቢኒያም መኮነን**
5. **ዳዊት ኪሮስ**

በ2009 ከ5ኛ አመት ተመራቂ ተማሪዎች በጥሩ አርዓያነት (ሞዴልነት) የተሸለሙ ሞዴል ተማሪዎች

1. **ኪሮስ ሀይለስላሴ**
2. **ሴቭየር ሚካኤል**

3. ዮናስ አለማየሁ

<u>በመልሳ ካፕ የዕግር ኳስ ጫዋታ</u>

ኮከብ ግብ አግቢ

- ❖ ሪያድ ሻፊ

ኮከብ ተጫዎች

1. እሱባለው 1ኛ አመት
2. ታምሩ 4ኛ አመት
3. በሪሁን 1ኛ አመት
4. ታደሰ 4ኛ አመት

ምርጥ አሰልጣኝ

- ❖ መሳይ 4ኛ አመት



የአንደኛ አመት የህግ ተማሪዎች ካሸነፉ በሗላ ደስታቸውን ሲገልፁ



የ3ኛ አመት የህግ ተማሪዎች በባህር ዳር ከተማ ጣና ላይ አባ ቸኮል ደሴት

ካምናው ካልተማርን

© በቃለአብ ይርጋለም

እንደ ተለመደው በዛሬው የወቅታዊ የወሬ ማዕዳችን እስቲ አንዳንድ ነገሮችን እናንሳ... ለዛሬው በሰሞኑ ዓለምም ሲያነጋግር ሰለቆየው UNICEF ባወጣው መረጃ ላይ በመመስረት ብናወጋ ምን ይመስላችል?

እንደምታውቁት ሀገራችን ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ዓመት የታሪክ ባለቤት እንደሆነች ለብዙ ዓመታት ሲነገረን ቆይቷል፣ ተያይዞም ለቁጥር በሚያዳርግ ሁኔታ የብዙ ግዜ በድርቅና በረሀብ ስሟ እስከ አሁንም ሲጠራ ሰምተናል እንደውም በአንዳንድ መፅሀፍቶችም ላይ ሟምር Famine የሚለው ቃል ኢትዮጵያን እንደምሳሌነት ሲጠቀሙ ያየነው ነገር ነው፡፡ እንግዲህ "ጉድ" በሉ፡፡ ይህ ከሆነ ከብዙ አመታት በኋላም በድርቅና በረሀብ ስማችን ዳግመኛ መጠራቱ የሚገርም ጉዳይ ነው፡፡

ለብዙዎቻችን የድርቅና የረሀብ ነገር ሲነሳ ቀድሞ የሚመጣልን የዝናብ ዕጥረት እና ተያይዞ የአየር ንብረት ለውጥ ቢሆንም የዚህ የድርቅ እና የረሀብ ምክንያት እንደተለመደው የተፈጥሮ የመጣ ነገሮች እንግዳ ሆነው ግን የሰው ሰራሹም ነገሮች የአብላጫውን ድርሻ እንደሚይዙት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከተፈጥሮ የመጡ ምክንያቶችን የምናይበት ጊዜ “a negative Indian ocean Dipole (IOD) ውጤት እንደሚያሳየው የምስራቅ አፍሪካ እንዲዘንብ ከሚጠብቀው አማካኝ የዝናብ መጠን በታች መመዝገቡ የተከሰተው ድርቅ በሶማሌ ክልል በዘጠኙም ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ በቦረና፣ ጉጂ፣ በምስራቅ ሀረርጌ፣ ከደቡብ ህዝቦች በኦሞ፣ ጋሞ ጎፋ እና አስገን አካባቢዎችንና አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮችን እንደጎዳ ተጠቅሷል፡፡ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ግዜ 5.6 ሚልዮን የሚሆነው በአካባቢው ላይ የሚኖሩ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሚባል የምግብ ዕጥረት እንዳጋጠመ ተጠቅሷል፡፡

UNICEF በሰሞኑ ባወጣው መረጃ መሰረትደም ለአሁኑ ወቅት 5.6 ሚልዮን የሚሆኑ ህዝቦች ምግብ አቅርቦት እንደሚያስፈልጋቸው፣ 303,000 ሺህ የሚሆኑ በአካባቢው ላይ የሚኖሩ የንፁህ ውሃ አቅርቦት እና 1.2 ሚልዮን የሚሆኑ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ልጆች ወደ ትምህርት ገበታቸው መግባት እንዳለባቸው አሳውቋል፡፡

ለብዙ ዓመታት የድርቅና የረሀብ ምክንያቶች ከተፈጥሮ ጉዳዮች ጋር ማያያዝ የተለመደ ቢሆንም እውነት የተፈጥሮ ሁኔታዎች ብቻ ለዚህ ሁሉ ተደጋጋሚ ድርቅና ረሀብ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ? እንዴትስ እና ለምን በተደጋጋሚ ይከሰታል? የሚል ጥያቄ መቼም በሁላችንም አዕምሮ ውስጥ ሳይፈጠር አይቀርም፡፡ ለዚህም ነው የሰው ሰራሽ ምክንያቶች ካለ ማጤን እና መመርመር አስፈላጊ የሆነው፡፡

ከሰው ሰራሽ የመጡ ምክንያቶችን ስናይ በሰሞኑ የ “Gurdian” መፅሔት የአየር ንብረት አጥኚው “Damien Carrington” ባወጣው ዕሁፍ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ 7 ሚልዮን ሄክታር መሬት በውጭ አገር ባለሀብቶች የተያዘ ቢሆን ይህም ማለት ከአውሮፓዊ አገር ቤልጂም ስፋት የበለጠ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ይህን የመሰለ ለምና ስፋት ያለው መሬት ለሳውዲ አረብያ እና ለህንድ ባለሀብቶች ባለይዞታነት ስር እንደሚገኝ እና ምርቱም ወደዛው እንደሚላክ አሳውቋል፡፡ በርግጥ ምርቱ ተልኮ የሚገኘው ገቢ አገራችን እንደምትጠቀም ቢታወቅም ግን ይህን ያህል ስፋት ያለው እና ለም

መሬት መስጠት በነዚያ አካባቢዎች ላይ ያሉትን ሰዎችን ማፈናቀል ብቻም ሳይሆን በዚህ መሬት ላይ በአርሶ አደሮቹ የሚመረተውን የእህል አቅርቦት እና የምግብ ፍላቶብ በእጅጉ እንደሚቀንሰው ይታወቃል፡፡

በዋናነት ግን ደካማ የስራ ባህል ጓላቀር የግብርና ዘዴ አማራጭ የሰብል ምርቶችን እና የምግብ አማራጮችን አለመጠቀም አላስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ ክንውኖችን /ድግስና፣ ተስካር/ ማብዛት፣ በመንግስት በኩል የተዛባ የመሬት ፖሊሲ እና አሰራሮችን መተግበር እንደ ዋና ዋና የሰው ሰራሽ ምክንያቶች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ችግሩንም እንዳይጠፋ ይባስ ብሎም እንዲጠናከር መንገድ ከፍተውለታል ባይ ነኝ፡፡ እንደ ምሳሌነት ለአንድ ወቅት በሀገራችን ሚዲያ የቀደምቱን የገጠሩን የግብርና ስርዓት የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስል ሲከታተል (እንደኢጋጣሚም ቢሆን እናንተም አይታችሁት ይሆናል) አንድ ገበሬ ሁለት በሬዎች ላይ ሞፈርና ቀንበር አድርጓል በፉጭትና በዜማ እያሞካሸ መሬቱን ይሰነጥቃል ከዛም አልፎ ወደ ሰማይ አንጋጦ የእግዜርን ውሃ ይጠብቃል፡፡ እኔን የገረመኝ በዚሁ ዘመን ያ ሁሉ ዘመን አልፎም የዛ ገበሬ የልጅ ልጅ የሚሆን ሰውዮ ያው ሁለት በሬ፣ ያው ሞፈርና ቀንበር፣ ያው ዜማ፣ ያው ተስፋን የየጠበቀ በእውኔ ማየቴ ነው፡፡ እኔ የምለው የኛ አገር ገበሬ አስር ብር ላይ ብቻ ነው እንዴ በትራክተር የሚያርሰው?

እንዲያው ነገሩ ነው እንጂ ጨሌስ ሰው አይጎዳም እንዳትሉ፤ አበው እኔም መዲጋገሙ፣ ካለፈው ትምህርት አለመውሰዳችን ነው እንጂ መራብስ ሁሉም ተርቦ አልነበር፡፡ ለምሳሌነት 1958-1961 የተከሰተው ትልቁ የቻይና ረሀብ 45 ሚልዮን የሚሆኑ የቻይና ህዝብ ህይወት ቀጥፎ አልፏል ነገር ግን ባደረጉት ከባድ የባህል ለውጥ ረሀብንና መከራን የአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከአገራቸው አስወጠድል፡፡ እኛም የሚጠቅመንን ለመያዝ የማይጠቅመንን እና ወደ ኋላ የሚጎትተንን በመተው ከአንጉል ባህልና ወግ ወጥተን ወደፊት ማንም የማይራብባትን አገር ለመፍጠር የሁላችንም ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን በመጠቆም ልሰናበታችሁ፡፡



የአምስኛ አመት የህግ ተማሪዎች የእግር ኳስ ቡድን፡፡

Good Bye



አንደኛ አመት 4ኛ አመትን በሪጎሪ አሸንፈው ዋንጫ በልተው በጭፈራ ላይ ፡፡



የመልሳ አመራሮች ከጎንደር የህግ ት/ቤት የተማሪዎች ማህበር አመራሮች ጋር ከስብሰባ በሁኋላ የጋራ ፎቶ



የ5ኛ አመት የህግ ተማሪዎች የመጨረሻ ጫዋታቸውን ሊያደርጉ ሲሉ



የአንደኛ አመት የህግ ተማሪዎች ካሸነፉ በኋላ ደስታቸውን ሲገልፁ

Free thinking for better future

የፋይፀፅ ራዕይ

ቁጥር-1

ምዕራፍ አንድ

አስማተኛዋ መንደር

@በፍፁም አብርሀም

መንደሩ ምን ዓይነት ገፅታ እንደነበረው መግለፅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ልክ በፊዥት ተሞልቶ እንደታፈነ ሙዚቃ ነበር፤ ዘፋኙ ማነው፣ አድማጩ ማነው፣ አጃቢው ማነው፣ ሙዚቃውስ ምነ ዓይነው ነው ሁሉንም ነገር ለይቶ ማወቅ ያስቸግር ነበር፡፡ ሰማዩ ላይ የነበረችው ፀሀይ እንኳን በርሀኑዋን ለማን ማብራት እንዳለባት ተወዛግባ ነበር፡፡ አይ ለሁሉም ልለግስ እንዳትል እንዴት አድርጋ፣ ምክንያቱም ብርሀንን ተከትሎ ጨለማው ይመጣል፡፡ በዚህች መንደር ያው ደስታ እንደ ዶሮ እንቅልፍ ነበር፡፡ ደስታህን አጣጥመህ ሳትጨርስ ሀዘን አቤት ይልሀል፡፡

በቃ የመንደሩ ታሪክ የተገነነው በሁለት ተፃራሪ ሀይሎች ቅብብሎሽ ነው፡፡ ገና የሀሴታቸውን አየር እየተነፈሱ፣ ልክ ወተት ላይ እንደሚቀላቀል ቡና፣ ሀዘን፣ ችግር፣ ረሀብ፣ መከራ፣ ድንቁርና፣ ሞኝነት የጥላቸውን አቅጣጫ እየቀየሩ ያጣላሉ፡፡ በእርግጥ ይህ ድባብ በሌላም ብዙ በመንደሩ አቅራቢያ ባሉ ሰፈሮችም ተመሳሳይ እይታ እንዳ፣ ከመንደሩ መግቢያ ላይ ጥሎኝ ካፊው ግስ አጠገብ ያገኘውት ወጣት አጫውቶኛል፡፡ ዳሩ ግን እኚህ መንደር ከሌሎች መንደሮች ብዙ የሚለዩዋ ምትሀቶች ነበሩ፡፡

መንደርዋን በጥልቀት እና በተመስጠ ለመረዳ ከገዛውበት የእይታ እያ የሀሳብ ቅኝት በመንቃት ራቅ ብሎ፣ የሀሳብ ይሁን የቁስ ገርዋገዋ ላይ የተቀመጠውን ወጣት፣ ስለመንደሩ ማወቅ እንደምሻ ነገርኩት፡፡ እሱም በቆሻሻ ከታጀቡት ጣቶቹ መሀል ጠቋሚ ዋጋ በማንሳት፣ በጭቃ እና በደለል ከተቆለለች ማማ ላይ ወዳለ ክብ ነገር ጠቆመኝ፡፡ እዛ ክብ ነገር ውስጥ ማወቅ ያብኝን ሁሉ ሊያሳውቀኝ የሚችል ሀቅ እንዳለ ውስጤ አመነ፡፡ ሁሉንም ሚስጥር ለማወቅ ካለኝ ጉጉት የተነሳ ጭቃው እና ደለሉ ላይ በግረኝ ኮማማው ላይ ወዳለው ክብ ነገር ተጠጋው...ክቡ ነገር ውስጥ ጠለቅ ብሎ ብዙ መንገላታት፣ መሰቃየት፣ እንደውም በግድ የለሽ ሰው የያዘ ሚመስል መጽሀፍ ነበር፡፡ መፅሀፉን ስመለከት ማን ስለ ምን ምን እንዳደረገው ለመረዳት ስለተቸገርኩ ውስጡን ለማየት ጉጉት አደረብኝ፡፡

ከመፅሀፍ ላይ ያለ ሀሳብ እና ያለ ግድ የለሽነት የተንተራሱትን፣ እሾህማ እና ተዋጊ ቅጠሎች ገፈፍ አድርጌ መግለጥ ብጀምር....ብገልጥ...ብገልጥ ባዶ ገፅ ብቻ፣ ግን ሁሉም ገፆች ውስጥ ደብዘዝ ባለ መልኩ የሚታይ ምስል መሳይ ስዕል እይታዮ ውስጥ ገባ፡፡ ምስሉ ግን ልክ ከየት እንደተጀመሩ በማይታወቁ መስመሮች ነበር፡፡ ምስሉን ለመረዳት በማደርገው ስቃይ መሰል ምርምር ውስጥ አትድከም የሚል ድምፅ ከወጣቱ አንደበት ሰማው፡፡ ፊቴንም ወደ ወጣቱ በማዞር ከገፅታው ላይ ከተከተቡት እውነታዎች ያለመድከምን ምክንያት አነበብኩ፡፡

ለካ እዚህች ማማ ላይ ከእኔ በፊትም፣ በኃላም ብዙዎች ነዋሪዎች እና መጤዎች እንደሚመላለሱ ተረዳሁ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ወደዚህች መፅሀፍ የሚጠጉት የራሳቸውን መነፅር ይዘው እንደመምጣታቸው፣ ከመፅሀፍ የሚያገኙትንም ሚስጥር ልክ እንደነሱ አይነት መነፅር ለተጨናበተ ነበር ሚያጋሩት፡፡ ማንም መፅሀፉን አንብቦ በሚያምንበት ነገር ላይ ያውለዋል፡፡ ይህ ደግሞ መንደር ውስጥ በውል ተለይተው በማን እንደተተከሉ በማይታወቁ እሾህማዎች እና አመኬላዎች የመንደሩን አዕምሮ አደንዝዘዉታል፡፡

ለካ ወደ እዚህች ማማ የሚጠጉት መንደርዋን ወደ ሰላም፣ ፍቅር፣ መተባበር፣ ብልፅግና ከፍታ ላይ ለማስቀመጥ ሳይሆን፣ አንዱ ከአንዱ ጋር ለመወቃቀስ፣ ለመፈራረጅ፣ ለመወነጃጀል ከተቻለም ለመገዛዛት ነበር፡፡ ስለዚህ አለኝ ወጣቱ፡- ስለዚህ ወደዚህች ማማ ላይ ብቅ የሚል ማንም ሰው የራሱን መነፅር ማውለቅ አለበት፤ አለበለዝያ መፅሀፉ እንደተዘገው ወንጌል ነው

ዳሩ ግን፣ የመንደሩ ነዋሪዎች ዝብርቅርቅ ባለ እና ውጥንቅጡ በጠፋ ማህበራዊ ሂደት እንዳለፉ መረዳት አያቅተኝም፡፡ ግማሹ የመንደሩ ነዋሪ ልክ አሪፍ የሳር ክምር ላይ እንደተኛ ሰካራም ተኝቶ ይቃዣል፡፡ ገሚሱ ማንን እና ምንን መከተል እንዳለበ ግራ ከመገባቱ የተነሳ እጀ ላይ ያለውን የህይወት ቁልፍ ጥሎ የሌላን ቁልፍ ለመቅረፅ ይሮጣል፣ ያስመስላል፡፡ በቃ በዚህች መንደር ከዛሬ ዉሎ አልፎ የነገን የኑሮ አላማ እና ግብ የሚያይ አይኖች ጠፍተዋል፡፡ ሳይፈልጉ የሚስቁ እና የሚያሸካኩ ጥርሶች በመንደርዋ ደምቀው ይታያሉ፣ ጦም ላለማደር ሚያሸገረድዱ ሆዶች ከገደል ሰፍተው ያስፈራሉ፡፡ የእዚህ መንደር ነዋሪዎች ዶፍ እየዘነበ በባዶ እርቃናቸው እና እግራቸው ሆነው ጐንጥላ ይለምኑ ነበር፡፡

ለዚህች መንደር አለንላት የሚሉ አንድ አንድ ነዋሪዎቹዋ እንኳን፣ ወይ የበግ አኮፋዳ ያጠለቁ ተኩሎች ናቸው ወይ

ተመሳሳይ ታሪክ የሚዘሩ ናቸው፤ ለዛም ነው እንደ ብልጭ ድርግም ብርሀን የመንደርዋ ንስሀ እየጠፋ ሚበራው፡፡ በዚህች መንደር ላይ የሚዘራው እና የሚታጨደው፤ የሚበቅለው እና የሚተከለው እሳት እና ውሀ ነበር፡፡ ለነገሩ ይሄ ለመንደሩ ትኩስ ጉድ አልነበረም፤ እንደውም አሁንማ የሚዘሩትንም እንዳያጡ የፈሩ ይመስላል፡፡

አሁን ሁሉም ነገር ተግልጦልኝ፣ በቃ የመንደሩ ነዋሪዎች በማን እንደተጨሰ በማይታወቅ አደንዛዥ ዕፅ ዘርዝዘዋል፡፡ የቁም እሬሳ ሆነዋል፡፡ ሚበሉትን፣ ሚጠጡትን፣ ሚለብሱትን፣ ሚያስቡትን፣ የሚኖሩበትን ምክንያት እንኳ በቅጡ አያውቁትም ነበር፡፡ ምክንያታዊነት እና ንቃተ ህሊና ሳይሆን ደመነፍስነት ራሳቸው ላይ ይታየኝ ነበር፡፡

ወጣቱ ልጅ ላይ በራ ጠፋ የሚል፣ በትዕግስት እና በባዶ ተስፋ መካከል እንዳ ዓይነት ድባብ አነብበት ነበር፡፡ ፍራቻ፣ አለማወቅም፣ ተስፋ መቁረጥም ወጣቱ ላይ እንደ ሰማይ መልህኩት የሚመላለሱም ይመስለኝ ነበር፡፡ ወጣቱንም የመንደሩ ጠባቂዎች ወደየአለ እነሱስ ምን ይመስላሉ ማወቅ እሻው አልኩት፡፡ እሱም ትዕዝብት በሞላበት አነጋገር እራስ ወዳዶችን ስለምን ከእኛ መሀል ትፈልጋቸዋለህ አለኝ፡፡ ግርምት እና ቁጭት ውስጤ ተላወሰ እንዴት መሪ እና ተመሪ እረኛ እና መንጋ በተለያየ መንደር ይኖራሉ በቃለዚህ መንደር ነዋሪዎች፣ ጠባቂዎቹ በሞት እና በህይወት መሀል እንዳ ፍጥረቶች ናቸው፤ አሉም የሉምም፡፡ ለካ እኚህ መንደርተኞች ነው ብለው በሚያስቡት እና እየሆነ ባለው ነገር መካከል ትልቅ በጣም ትልቅ ከተልባ እና ኮምሳስ የተሰራ ሚመስል ግንብ ነበር፤

የግንቡ መሰረተ ድንጋይ የተጣለው በተለያዩ ፀጉረ ልውጦች እና በጠባቂዎቹ ነበር፡፡ መንደር ውስጥ እንዲሰማው ጭምጭምታ ግንቡ ወደ 3000 ዓቱ ነው የሚሉ አሉ፡፡ የመንደሩ ነዋሪም ግንቡን

አልፎ ካው ቦታ መግባት እንደሚፈልግ እና ከግንቡም ጀርባ የመንደርዋን ህመም /ደዌ/ የሚያክም ፈውስ እንዳለ ያምናሉ፤ ለዛም ብዙዎቹ የኑሮዋቸውን እንቅስቃሴ ግንቡ ላይ ካሉት ሞላስስ እና ተልባ ጋር መጨማለቅ ነበር ….ሁላ ቤተ አምልኮ ግንብ ስር ቁጭ ብለው የህይወታቸውን መለወጥ ከአንዳች ተዐምር እንደሚጠብቁ ተመፅዋቾች ጥቂት ማይባሉ መንደርተኞች ከምታህተኛው ግንብ ስር ቁጭ ብለው እጣ ፈንታቸውን ሚወስንላቸውን ሀይል ይጠብቃሉ፡፡

ይህም ነገር ከማውቀቅ ትልቅ እውነት ጋር ተጋጨብኝ፤ እንዴት መንጋ እረኛውን ፍለጋ እንደዚህ ይደክማል፡፡ ከወጣቱ ጋር እንቀዝፈው ከነበረው ባህረ ሀሳብ ላይ ታዲያ እሺ የመንደሩን ደዌ ፈዋሽ ዕፅ ወደየት አለች የሚል በግራ ዛቢያ የተሞላ የወጣቱ ጥያቄ አነቃኝ፡፡ ግን ብነቃም ለወጣቱ ምላሽ አልነበረኝም፤ ነገሩ የገባው ወጣትም ተመሳሳይ ሪት አሳየኝ፡፡

ዐይኖቼንም ከግንቡ ጀርባ ሳይሆን፤ ከመንደሩ በስተምስራቅ በኩል ራ ብሎ ከሁሉም በላይ በዛ መንደር ውስጥ የፈካ ሰባት ትላልቅ ፍሬ ያሉት ዛፍ መሰል ተክል ላይ አረፉ፡፡ ተክሉ ግራ ሞገሱ ልክ እንደ ህይወት ዛፍ ነበር፡፡ ስለተክሉም የሚያውቀው ነገር ካለ ወጣቱን ጠየኩት፤ ወጣቱ ግን ሰለምን አይነት ተክል እንደጠየኩት አይደለም ተክሉንም የማየት ዓይነዳና አልነበረውም፡፡ ግን እንዴት እየተከሰተ ያለው ነገር አልገባኝም፡- የወጣቱን ዓይነ ዳና የገረደው ሞራ ምን ይሆን ወጣቱ ብቻ አይደለም መንደርተኛውስ ስለምን ይህን ተክል ማስተዋል አቃታቸው ምናልባት እኔ ወደዚህች መንደር የመጣው እንግዳ ስለሆንኩ ይህን የታየኝ ነው ወይስ እኔም እንደ መንደርተኛው የቅዠት ባህር ውስጥ እየሰረኩ ነው ይህስ ተክል /ዛፍ/ የያዘው ሚስጥር እና ሀይል ምን ይሆን

ይቀጥላል……



የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት የተማሪዎች ማህበር መቐለ መጥተው ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት የተማሪዎች ማህበር ጋር የደረጉት የእግር ኳስ ጫዋታ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ት/ቤት የተማሪዎች ማህበር አሸናፊነት ሲጠናቀቅ……..



መልሳ ካፕ የሽልማት ስነስርዓት የዓዲ ሓቂ የስፖርት ተጠሪ ተወልደ ሽልማቱን እየሰጠ

በጦርነትም ህግ አለ

© በሀሸን

ታሪክ ነግሮናል፣ እኛም እየሰማን እያየን ነው፣ ቀጣይስ?

በዚህች ምድር ከተደቀኑብን አያሌ ፈተናዎች መካከል መፍትሄ ልናበጅለት ያልቻልነው እያቆሰለን፣ እያደማን፣ እያሰቃየን፣ እየበላን፣ እየቀረጠፈን ያለው ጦርነት ነው። በታሪክ እንደምናውቀት፣ ይህቺ የምንኖርበት ዓለም ከጦርነት አረንቋ፣ ሰቀቀን ለአንዴና ለአፍታ እንኳ አርፋ አታውቅመም። ሁሌም በሰው ልጅ ዘመን ጥላቻ፣ ግጭት፣ እርስ በእርስ መናቆር ብቻ ጦርነት መለያም፣ መሳሪያም ሆኗል።

ህፃናት፣ እናቶች፣ አዛውንት፣ ወጣት ምንም ሳይለይ እስከ አሁን እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ ጦርነት በቢሊዮን የሚቆጠር መዓት ሰው በልቷል። ህይወታችንን አመሰቃቅሎ ትልቀ ጠባሳ ጥሎብን፣ ተፍቶቡን፣ ዘንቦብን ከመሄድ መቼም ተቆርጦ አያውቅም። በዚህ ረገደ በቅርቡ ከ1914-1918 እ.ኤ.አ የአንደኛ እና ከ1939-1945 እ.ኤ.አ የዓለም ጦርነት ትልቅ ምስክሮቻችን ናቸው። ነገር ግን በጦርነት መስክ ከሁሉም በላይ የሚዘገንነው ነገር በጦርነት ውስጥ ተሳትፎ የሌላቸው፣ ለምሳሌ:- ህፃናት እና እናቶች ለአንዴ እንኳን ሳያመነታ ህይወታቸውን ቀርጥፎ መብላቱ ነው።

ለመሆኑ ጦርነት ማለት ምን ማለት ነው፣ እንዴትስ ሊከሰት ይችላል፣ በማን መካከል የሚካሄደ ነው?

ጦርነት፣ ይሽ ነው ብለን በውል መናገር ባንችልም፣ ነገር ግን የአንድ ግጭት ውጤት መሆኑ ያለ አንዳች ጥርጣሬ መሆን እንደልባችን ልናወራለት የምንችል የበሰለ ፍንክች የማይል እውነት ነው።

ጦርነት በመንግስታት መካከል፣ በታጣቂ ሃይሎችና መንግስት ወይም በታጣቂ ሃይሎች መካከል የሚካሄድ ሊሆን ይችላል። መንስኤው የተለያየ ቢሆን እንኳን አንድ መግባብያ ላይ መድረስ የምንችልበት ነገር ቢኖር ጦርነት የግጭት እና ግጭት ውጤት መሆኑን ብቻ ነው። በዚች ዓለም ሁለት የተለያዩ ፍላጎቶች እስካሉ ድረስ ግጭት ልናስወግደው እና ልናጠፋው አንችልም፣ ግን የሚያስከትለው አስከፊ ውጤት መቀነስ ይቻላል። እንዴት?

የትያትሩ ደራሲያን እነማን እንደሆኑ ቀደም ሲል አይተናል። እነሱም መንግስት እና ታጣቂ ሃይሎች ወዘተረፈ.... ናቸው። በነዚህ ደራስያን ተመርጦ ለትወና የሚቀርቡ ደግሞ ወታደሮች ናቸው። ከእነዛ ውጭ ያለ ሁሉም ሰው የዛ ትያትር ተመልካች ከመሆን በስተቀር በትያትሩ ምንም፣ ግን ትወናው እንዳመጣ ተዋናይ ተመልካች እንደሚሆነው ሁላ ወታደር ቆስሎ ከውግያው ሜዳ ከወጣ ወይም እጅ ከሰጠም እንደ ሲቪሊያን ነው የሚቀጠሮው። ወደ ጦርነት መርሕ አምጥተን ስንመነዝረው ደግሞ የአንዱ ጦርነት አካል መሆን የሚችሉ አዛዦችና ተዋጊ ወታደሮች ብቻ ናቸው የተቀረው ሰፊ ህዝብ እና የቆሰለ ወታደር ወይም እጅ የሰጠ ከጥቃት መጠበቅ አለባቸው። ስለዚህ በነዚያ የጦርነት ውግያዎች አካል የሆኑ ብቻ ነው የጦርነት ሰለባ መሆን ያለባቸው። ምክንያቱ ሊበድሉህ እየመጡ ዳቦ ላጉርሰህ ግደሉኝ ልትላቸው አትልችምና። ነገር ግን በጦርነቱ ምንም እጅ የሌላቸው እና የቆሰሉ እና የተማረኩ መግደል እና ማሰቃየት ሰብኣዊነትን የሚቃረን ትልቅ ወንጀል ነው። በአጭሩ ስለ ጦርነት ባህሩ Jean Jacques Rousseau እንዲህ ይለናል

“War is in no way a relationship of man with man but a relationship between states, in which individuals are which only by accident, not as men, nor even as cities, but as soldiers...since the object of the war is to destroy the enemies of state, it is legitimate to kill the letters defenders as long as they are carrying arms but as soon as they lay them down and surrender, they cease to be enemies on agents of the enemy and again become mermen and it is no longer legitimate to take their lives” ለዚህም ነው የዓለም መንግስታት በ1949 እ.ኤ.አ በ Geneva Convention አራት conventions ያፀደቁት እነሱም

Geneva Convention I and II በጦርነት ሜዳ የቆሰሉ፣ የታመሙ ከለላ የሚሰጥ ሲሆን፣ Geneva Convention III ደግሞ እጅ ለሰጡ፣ ለተማረኩ ከለላ የሚሰጥ ሲሆን፣ Geneva Convention IV ለሰፊው ህዝብ፣ ለሲቪላን ከለላ እና ጥበቃ የሚሰጥ ነው

ሠላም እንሰንብት!

የጨንቻው ሊቅ

© በብሩክ ተስፋዬ

Biruktesfaye181@gmail.com

"ሞት አይሙት ምን ጊዜም ግን አይሁን ገልቱ የማይሞቱ አይግደል ሳለ የሚሞቱ"

አያልነህ ሙላት ይችን ስንኝ የቋጠረው ለነ-ጋሼ አሰፋ ጫቦ ላሉት ልበ ብርሃን

ኢትዮጵያዊያን ይመስለኛል፡፡ ጋሽ አሰፋ ለዘመኑ ወጣቶች እንደአብሪ ኮከብ ሊታይ የሚገባው ምርጥ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ከዘረኝነት ቀይ መስመር ያልታጠረበ ወሰን ጡብ ያልተከለለ እንደሆነ የሚያረጋግጥልን አንዱ ጋሽ አሰፋ ነው፡፡

ጋሽ አሰፋን ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋወቀን (ለዘመን ተጋሪዎቼ ለማለት ነው) አንድ የሳተላይት ጣብያ ነው፡፡ አሰፋን ለመጀመርያ ጊዜ ላየው ያነጋገር ለዛው፣ በተለይ ያተራረክ ውበቱ ከተለመደው ያተራረክ ይትብሐል ይለይበታል:: የአሰፋ ትርክት ከመሠረቱ (from the ground) ፍሰቱን ጠብቆ የሚሄድ ያተራረክ ዘይቤ ያለው ሰው ነው፡፡ ይሄን ዘይቤ የታደሉት ደግሞ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ይመስሉኛ (እኔ እስከማውቀው ዶ/ር እጓለ ገብረ-ዮሐንስ አንዱ ናቸው፡፡)

የጋሽ አሰፋ በአስኳላው ትምህርት የህግ ዲግሪውን ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩንቨርስቲ ወስዱዋል፡፡ አሰፋ በዩንቨርስቲ ተማሪነቱ ወቅት በአሜሪካ ሀገር በተዘጋጀው ዓለም ዐቀፍ የሙት ኮርት ውድድር ኢትዮጵያን ወክሎ አሸናፊ ሆንዋል፡፡ አሰፋ የዚያን ጊዜ ትዝታ ሲናገር "ውድድሩን አሸንፌን ከመጣን በኃላ ከቤተ-መንግስት ጥሪ መጣልን ጃንሆይ ጋር እጅ ነስተን ለሽልማት ቀረብን ከዚያ ጃንሆይ "ከነማን ጋር ተወዳድራችሁ አሸነፋችሁ አሉን ?" አንድ ቀደም ቀደም የሚል አብሮኝ የተወዳደረው ጓደኛዬ ከዓለም ከመጡ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ጋር አለ፣ በዚህም ጊዜ ጃንሆይ እንደመገረም ብለው፣ "እንግሊዞችንም?" ብለው ጠየቁን እኛም "አዎን ጃንሆይ" አልናቸው፡፡ ወስላቶች ብለው የወርቅ ሰዓት እና ገንዘብ ሰጥተውን አሰናበቱን "

አሰፋ የስልሳዎቹ ትውልድ ቢሆንም ከብዙዎቹ የተማሪ እንቅስቃሴ መሪዎች ጋር ጓደኛ ነበር፡፡ በእንቅስቃሴው ግን አሰፋ እንብዛም ተሳታፊ ግን አልነበረም፡፡ አብዮቱ ከፈነዳ በኃላ ግን ወጣቱ አሰፋ በኢትዮጵያ ፖለቲካ መሪ ተዋንያን ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ሆኖ ነበር፡፡

ጋሽ አሰፋ እራሱን የዘውትር ጊዜ ጸሐፊ ነኝ ባይልም ግን እንደሚለው "ብልጭ ሲልብኝ እጽፋለሁ!" ይላል፡፡ ጋሽ አሴ ብዙ ለመፅሔትና ለጋዜጣ የሚሆኑ መጣጥፎችን አበርክቷል፡፡ በመጽሐፍ ደረጃም ባለፈው ዓመት ያሳተመው የትዝታ ፊልግ የተሰኘው መጽሐፉ ተጠቃሽ ነው፡፡

ይሔን ሰው ነበር ሰሞኑን በሞት ያጣነው፡፡ አንድ ወዳጄ እንዳለው ጋሽ አሰፋ መታመሙን ስሰማ እንኳ ወኔው እና የወጣትነት መንፈሱ፣ በዓይኔ ድቅን እያለብኝ፣ ሕመሙን ዘረኞችን እንደሚደፍቀው መንፈሱ አሸንፎት እንደሚነሳ ቅንጣት አልተጠራጠርኩም ነበር፡፡ ግን ሁሉን ለሚገዛው ሞት በመጨረሻው ጋሽ አሰፋ ተሸነፈ፡፡ ኢትዮጵያዊነት ከጎጠኝነት እና ከመንደርተኛነት በላይ ለሆነላቸው ሁሉ ዛሬ የመረረ የሀዘን ቀን ነው ኢትዮጵያ እጅግ የሚወዳት ልጇዋ ሳይሳለማት በሩቅ እንደናፈቃት እንደተሟገተላት ሲለያት ምን ይሰማት ይሆን ሲል ነበር የጋሽ አሰፋን ሞት በሀዘን የገለፀልኝ፡፡ በመጨረሻም ባለቅኔው እንዳለው "እርግማን ሆኖብን በሀበሻ ምድር ላይ ደግ አይበረክትም፣ አይበረክትም"

ነፍስ ይማር፡፡

ብልጥ ከሰው ስህተት ይማራል ሞኝ ግን ከራሱ ↔

ላንዴ...!

© በአንተነህ ዘሪሁን

contemporaryanteneh@gmail.com

...እንዲህ እንዲህ እያልኩ ተመናቃሪነትን፣ በጥላቻነትን እሰብካለሁ... ማጥራት ያቃተው እንኳ የመበጥበጥ አሃዱ ሲያበስር የለውጥ ጥንስስ በቀዳማይነት ከህሊናው ተሟሯልና--- ከምስጋና ችሮታችን ትንሽ ብናካፍለው `ምንም` አይለን... ዛሬ ውጥንቅጥ "ቀደዳ" እቀዳለሁ፣ አጥርቶ [አንዳንዴም የመገጣጠም ብሂል የገባው፣ ገጣጥሞ] ለመረዳት የተጋ ቃላት ማሳቀቁ ውስጥ ትርጉም የሚያጣ አይሆንም... ልባምነት ከ'ርኃታ አላኖረኝ ብላ_ማዕበሏ የሕልው ደርዜን እያጠበ፣ እያረጠበ የትውልድ ምዕልት ውስጥ - አስተውሎትን አጥቼ - እባክናለሁ... 'ብክነት ውስጥ ጣዕም የለም' የሚል ያልባከነ መሆን ይኖርበታል...

እንግዲህ... ተመናቃሪነት... በጥላቻነት... ምንድነው?

ዓይኔ ሥውረትን ይፈልጋል፡፡ ድብቅ የሰው ልጅ ሰዋዊ ተግዳሮትን፣ ስብዕና ላይ የተጫነ ሕፀፅን፣ ታክኮ አልለቅም ያለ ያንደበት አልያ የነፍስ ፎከት ላይ [ብቻውን ሳይሆን] ይንቀዋለላል፡፡ ጥቁምታዬ... የዘመኔ ምስል መዋጮ ነው... ጥበባዊ ክሂል እየለበድኩበት... ምንም ቢበርደኝም... ለእሳታም ዘመኔ አንድ የነገር ወርች እማግዳለሁ... ዓይኔ ከሁሉም የወጣውን_ጎልቶ የሚታየውን _ የወርች ፍም እታዘበ... ነድዶ ካላለቀው እሳት አልባ ነቁጥ ጋር አብሮ ይዘምራል... ያጠናል... ይቃኛል...

...በጥላቻነትና ተመናቃሪነት ለየቅል የመሰሉ እሳቤዎች ናቸው...

የግንኙነታቸው ስንጥቅ መስመር በጥበብ [ራሴ] እየፈጠርኩ __ ያልፈላ (በ'ርግጥ የበሰለ) ሃሳቤን ልወርውር... ተመናቃሪነት አንዲት የአስራአራት ዓመት ልጃገረድን ያስታውሰኛል... ትንንሽዬ አጎጠጎጨዎቿን በXXL የጡት ማስያዣ [የእናቷን ሰርቃ መሆን አለበት... ሀ.. ሀ.. ሀ] ተደብቃ የምትሞክር... በትንሽዬ መስተዋት እያጮለቀች ከንፈሯን የምታማታ... የፈገግታዋን ክበብ በታላቅ እህቷ [መቸም በሞናሊዛ የሚል ፈዛዛ አይኖርም ብዬ ነው...] የሳቅ አጀባ ጋር እያጣመረች የምትፈትን [‹ውበት ተፈታኝ ነው› ብላስታምን]... የአስራአራት ዓመት ኮረዳ ትውስ ትለኛለች፡፡ ... ተመናቃሪነቷ የሚጀምረው ተደብቃ ከምታየው መስተዋት ጋር ስትለያይ “ለሰዎች” የምትተው ነው ‹ሥርዓተ-ሴትነት ወእርምጃ› ላይ ነው፡፡ [የጓዳ ትንተናው ሙሉ ፈጠራ ነውና__ እህት በሌለው ዓይን ብትቃኙልኝ ምናልባት መግባባት ያውቀን ይሆናል]

እንዲያው ትንሽዬ በሆነች የግል ዓለሟ ውስጥ የምታደርገውን ‹እንከናም እሰጥ-አገባ› ተመናቃሪነት እላታለሁ... በጥቃቅንነቷ ግን ጉጉት ላንገበገባቸው የእድሜ እኩዮቿ ጎረምሶች... ምናልባትም ‹አላለፈብኝም› ለሚል ‘የጨረቀ ሼባም በስሱ ጎልቶ የሚታይ ይሆናል...

ሌላ “ደሴት ይጎችሁ ልሂድና... እንመለሳለን፡፡ (‹ፅላልህን አራግፍ ወዳጄ...!›)

* * *

...አንድ ናርሲሰስ የሚባል ጎረምሳ በዱሮ ጊዜ ይኖር ነበር... [አሉ] ...እና ያኔ መስተዋት ባልነበረበት ዘመን __አንድ ቀን__ካንድ ምትሓተኛ ኩሬ ውስጥ መልኩን ተመልክቶ በፍቅር ይለከፋል... [ያኔ ፍቅርም ለካፊ ነበር]... መመናቀር ይሉት ይህን??? ናርሲሰስ እየተመላለሰ መልኩን ኩሬው ውስጥ ይመለከትም ነበር... [ሞት አይቀርምና]... ሞተ፡፡ [ምን፣ ለምን፣ እንዴት ሞተ? ዓይነት ‘ንዝንዝ’ ለጊዜው ይቆየኝ]... ብቻ ናርሲሰስ ሞተ፡፡ ያኔ ኩሬው በውሃ ፈንታ እንባ አቀረረ፡፡ አስተዛዛኝ በሽ ነበር መሰል... ሊያፅናኑት መጡ... “ናርሲሰስ መሞቱ በጣም ያሳዝናል፤ መልከመልካም ሰው ነበር...” አሉት፡፡ ኩሬው የናርሲሰስን በጥቃቅንነት እንዲህ ነበር የገለፀው -(በመልሱ)- “እኔ የናርሲሰስን ቁንጅና መች አይቼ አውቃለሁ፤ በናርሲሰስ ዓይን ውስጥ የራሴን መልክ፤ እንደመስተዋት፤ መመልከቴን ብቻ ነው የማውቀው፡፡ ታዲያ አሁን እሱ ከሞተ ራሴን በማን ውስጥ ልይ?” የኩሬው እንባ ጠብ ማለቱን [የት ጠብ እንዳለ] ታሪኩ አያወራም... (መሰለኝ)

* * *

በአስራአራት ዓመት ኮረዳነት ውስጥ ያደገች ሴትን [የማታድግ አለች’ንዴ _ ለሚል ዓለሙ ጠብባለችና ጥቂት የማስፋፊያ ግንባታን ከብዙኖች ልምድ ይገንባ...እላለሁ] ቅንዝሩ ያልበረደ ሼባ የሚመለከቱት ‘በጥቃቅንነቷን’ ባይሆን እንኳ ትውስታ መላሽ ትንግርትነቷን እንደሆነ ጠረጥራለሁ፡፡ “ሴትነትን” አፍስሶ ለማየት የበቃው ጭኗ ውስጥ መታሸትን ቢሻም፤ ያለመቻል ልጓም የሃሳቡን ቅያስ ያስቀይረዋል... እናም ያኔ__ ጊዜን በህሊናው ሸንቁሮች ውስጥ እያጠመደ ይመልሰዋል... ይመለከተዋል... ሰውነቱ ከከንፈር መንከስና በተጨበጠ እጅ ከሚሳበቅ ናፋቂነት ባይዘልም... የሞቀ ጭኑ በህይወት ትርጉም ፋታ እየወሰደ መርገቡን ለማወቅ የግድ እስክትሸመግሉ ጠብቁ አልላችሁም...

ሓሳቤ በጥቃቅንነትና ተመናቃሪነት ዙሪያ መንደርደሪያ እርካብ የምንራበት ቀጭን ማሰሪያ ልጥ ማበጀት ነው... [ባይሆንም የናንተ ጉብዝና በቂ እንደሆነ...]

ትንሽ ደሜ ሞቋል... የመኖር ፍትወቴን ትርጉም ቆርጬ መጣል የሚያስችል ተጋፋጭነት አያለሁ... ራሴ ውስጥ... ሰዎችም ውስጥ... ምክንያታዊነት ከሚተራመሱ ጓዶቻችን ምልዐት ውስጥ መሸለኪያ አጥቶ ዳር ይንጠራወዛል... የተጠጉትን “በሽተኞች” እያስባለ ብቻነቱን ያፀድቃል... እኛ፤ የተገጠብነው ይሁን ውበት ሆኖን የተውነው፤ ያላወቅሁት ነቁጢ ይኮሰኩሰኛል... ባህር ዐይቶ የማታውቅ ነፍሴን ‘ለቀዘፋ ተዘጋጂ’ እያለ ማርገብገቡ፤ መበጥበጡ ለምን ነው?... ያልጎደለበት አንገቱ ክሳድ ላይ ጨርቅ ካላፊ ነፋስ ከማስጣል የተሻለ ምን ምን ከለላ ያደርጋል... አቅጣጫውን ላለማስቀየር የተደነቀረ የመርገጫችን ታኮ ሆነ እንጂ፡፡ መበጥበጥ ይሉሃል ይህ ነው! ቀለም የሚቆጥር በጠፋበት ሁናቴ፤ ለህብረ ቀለምነት፤ መበጥበጥ መሻት ሃጥያትነቱ ለተመናቃሪያን ብቻ ይመስላል... መመናቀር ምልሰት ነው... ናርሲበስ በገዛ መልኩ በፍቅር መለከፉ... ራሱን ለመሻት ኩሬ ማጎንበሱ... ይህን ምንቅር አይሉት? በመስተዋት ኑሮ ውስጥ "መባከን" መመናቀር ይመስል፤ ከጥፋቱ ጋር አብሮ የመክሰም_የቅፅበት ምርጫ የአፍላ ኮረዳ ሴትነት ጋር ምሰለቱ ያፍታነቱ ርቀት ማጠር፤ የወሰን እብደት መሰለኝ... ለማንኛውም ናርሲሰስ ተመናቀረ እናም ከመልኩ ጋር በፍቅር ሲወድቅ የምትሃተኛው ኩሬም እንባ ይወድቅበት ቢያጣም አይኑ አጠላ፡፡ ብጥበጣው ይህ ነበር_ የናርሲሰስ...

[ዐሃፊው]... መሻቴም ይህ ነው... ከተሰራ ምናብ ውስጥ እናንተን እየተውኩ ይህን መቀመር... በፊደል ማርቀቅ [?] ማዕደቅ... ልቦናችሁ ላይ ላፍታ አዳሪ ሀሳብ መዝራት... ልንሰራት የጀመርነውን የእርካብ ማሰርያ ልጥ፣ የሃሳብ ግብ ግብ ውስጥ እየተሳቀቅን የመጨረስ ብልሃትን ማስላት... (በቃ እንድንመናቀር ነው)

ዓይኔ ሰውረትን ይፈልጋል... በየምናምን ጓዳችን የደበቅነውን ተግዳሮት... (ካርል ጀንግ እንደሚለው ግለሰባዊ ዕልመታችንን) ...የራሴን በመፈለግ ስባክን ዓይኔ ሥውረትን ያያል... በእያንዳንዱ ስብዕና ላይ መሰረቱን ያፀና ህፀፅዊ [ምልከታዊ ቡጉር ዓይነር ነገር] ...ታክኮ አልለቅም ያለ ያንደበት አልያ የነፍስ ፎከቴን ስፈልግ፣ ያን ሊያግባባን ዘንድ የማይመስል ያልተነፀረ ሥውረታችንን ዓይኔ በያፍታው ይፈትሻል... ሥመናቀር... ሥበጠብጥ... ዓይኔ ያውቃል... [ሳቅ]

ናርስሲዝም... [በርግጥ ከናርሲሰስ አይደለም_እወራረዳለሁ] ተጣብታናች... "እኔን ሰዎች ዐይን ውስጥ መፈለግ የዘመኔ ድርሰት አካል ሆኜበት፣ አመናቀረኝ... አበጣበጠኝ" የማስታወሻ ደብተሬ (ደብተራችሁ) ድርሰት ትሁን... ሁሌ ትውስ ትለን... መውጫ

ያ ኒቼ የሚባል ፈላስፋ [ማጥራት ሲያቅተው ሊበጠብጥ_ሲመናቀር] እንዲህ ብሎ ነበር...

“He, who has a ‘way’ to live for, can bear with almost any ‘how’!”

በነፃ ስንኝ ዜማ እንቋጨው

“እንድ የህይወት ጠያቂ

ለመኖር ለምን ባይ

እርሱ ነው ሁሉን ቻይ

ከዕልመትን በኋላ

ብርሃን ብቻ የሚያይ!”

ጥሁም ኑሮ!



የ2009 ዓ.ም የህግ ት/ቤት የተማሪወች ማህበር አመራሮች



3ኛ አመት የህግ ተማሪዎች ለመልሳ ካፕ ውድድር ዝግጅት ሲያደርጉ

ሞድዬል የህግ መምህር እና ተማሪዎች ምርጫ መስፈርት

እውቅና የሚገባው መምህር ከተማሪ ጋር መልካም ቅርርብ ያለው ለተማሪ የሚያስብ እና የተማሪን ችግር የሚረዳ ለተማሪዎች መልካም ስራን እየበረከተ ያለ ተማሪዎችን በማገዝ እንዲሁም ለተማሪዎች የሚቆርቆር በቻለው መጠን ሁሉ አስፈላጊው እገዛ እና ድጋፍ ለሚያደርጉ የህግ ሞድዬል መምህርዎን ይምረጡ የሚል ነብር፡፡

ቀጣይ የመልሳ የቤት ስራ

1. ሁሉንም ያካተተ ከሴት እና ከአይነ ስውራን ተወካዮችን ጨምሮ የህግ ት/ቤት የተማሪዎች ፓርላማን ማቋቋም
2. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና የምርጫ ህግ በተቋቋመው ፓርላማ ማፅደቅ
3. ፍሬሽ ዌልካም በጥሩ ሁኔታ ማዘጋጀት
4. የህግ ተማሪዎች ፓርክ ወይም ልዩ ክልል የህግ ት/ቤት ቦታ መንከባከብ እና መያዝ
5. ሙት ኮርት ወውድድሮችን ባዲስ መልክ ማስኬድ
6. የተቋቋሙትን ክለባት ማጠናከር
7. የመልሳ ካፕን ማስቀጠል
8. የሽኝት ፕሮግራሙን ማስቀጠል
9. ሎየርስ ናይት ማዘጋጀት
10. መልሳ ቮይስን ማጠናከር
11. የህግ ተማሪዎችን የነፃ ህግ ድጋፍ አገልግሎት ማስፋፋት
12. የመልሳ በግቢው ውስጥ ያለውን ጥሩ ተፅዕኖውን ማስቀጠል
13. ሴቶች የሚሳተፉበትን መንግድ መፍጠር
14. የሴቶችን ተሳትፎ በመልሳ እና በሌሎችም ፕሮግራሞች ማምጣት፡፡ እና ሌሎችም ስራዎች ከፊት ይጠብቁታል መለሳ.....መልካም ክረምት ለሁላችን ፡፡

መልካም ስራ ለከፉ ቀን ስንቅ ነው!!

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ዶክተር ክንደያ ገብረሂዎት የተገኙበት የመልሳ የአመቱ የፍፃሜ ታላቅ መሰናዶ

በሙሉ ልብስ ድምቅ ያሉ ጥቂትም የማይባሉ ትንሽ ጅኒና (Gentility) የሚያውቃቸው የዛሬ ተማሪዎች- የነገ የፍርድ አደባባይ አስተናባሪዎች በምስለ ችሎት አዳራሽ አልፈው አልፈው ተቀምጠዋል:: በጣት የሚቆጠሩ ሴት ተማሪዎችም በመሀከላቸው ይታያሉ: የት/ቤቱም ቁንጮ መምህራን የሀበሻ አረፋፋድ አርፍደው መምጣት ጀመሩ ከአፍታ በኋላ ዝግጅቱ ተጀመረ

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ክቡር ዶክተር ክንደያ ገ/ሂዎት የተገኙበት ልዩ የሽኝት ፕሮግራም ለአምስተኛ አመት ተመራቂ የህግ ተማሪዎች በዕለተ ቅዳሜ 24/10/2009 ዓ.ም በህግ ት/ቤት የሙት ኮርት አዳርሽ ከጥዋቱ 3፡00 የጀመረው ይህ ፕሮግራም በህግ ት/ቤት በአይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን ከዚያም አልፎ ብዙ አዳዲስ ድንቅ የሚባል ክስተቶችን አንግቦ ነበር፡፡ ፕሮግራሙ በአምስተኛ አመት ተመራቂ የህግ ተማሪ ሱራፌል ሲመራ በህግ ት/ቤት የተማሪዎች ፕሬዘዳንት ሚኪያስ መላክ ፕሮግራሞችን በማስተዋወቅ እና በእንኳን ደህና መጣችሁ መልክት በማስተላለፍ የመክፍቻ ንግግር በህግ እና ስነ-መንግስት ኮሌጅ ዲን በክቡር አቶ ገብረሐዎት ሐዱሽ እንዲከፈት በመጋበዝ የዕለቱ ዝግጅት ተጀምሯል፡፡ ክቡር አቶ ገብረሐዎት ሐዱሽም ፕግራሙ ከከፈቱት በኋላ የአምስተኛ አመት የህግ ተማሪዎች የአምስት አመት ቆይታ በዕስላይ ለተዳሚዎች ለዕይታ ቀርቧል፡፡ ከዕስላይድ ቪዲዮ ቆይታ በኋላ በህግ ተማሪ አንተነህ ዘሪሁን በኩል ግጥም ቀረበ፤ ግጥሙም በሁለት የተከፈለ ሲሆን አንደኛው አደራ የሚል ይመስል ነበር ስው እዳታጉላሉ፤ አልጋ ባልጋ አጠብቁ፤ ጨርቅ መንገድ አትናፍቁ ወ.ዘ.ተ ነበር፡፡ሁለተኛም ግጥም በሙዚቃ ታጅቦ ቀረበ ከዚያም ምርጥ የአመቱ ሞዴል ምምህራንን ሽልማት በሚኪስ አቅራቢነት በተመራቂ የአምስተኛ አመት ህግ ተማሪ ኦምኔል ሽልማቱ አንድ በአንድ ስማቸው እየተጠራ ለ5 መምህራኖች የምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

ከተሸላሚ መምህራኖች ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው አቶ ገብረአብዝጊ ወልደስላሴ ንግግር አድርገዋል በንግግራቸውም በጣም ደስ እዳላቸው ገልፀዋል፡፡

በመቀጠልም በአስተዳደር መልካም ግንኙነት እና እገዛ እያደረጉ ያሉ ስዎስት መምህራኖቸች ተሸልመዋል እነሱም

1. አቶ ገብረሂወት ሀዱሽ
2. ምህረተአብ ገ/መስቀል
3. መብርሀቶም ፊቲው

ከማተዳደር ባለፊ በማስተማር ሙሉ ጊዜያቸው ለተማሪ በመስጠት እና ለተማሪ በማሰብ እያደረጉት ላለው መልካም ተግባር ጎሽ በርቱ የሚያስብል ነው ሲል ሚኪያስ ያለውን ክብር እና አድናቆት በመደናገጥ ተናግሯል፡፡

ተማሪዎችም የተሸለሙ ሲሆን ሽልማቱም እንደሚከተለው ነበር፤

በ Exit ከፍተኛ ውጤት ያመጣ በአካዳሚክ ከፍተኛ ውጤት ያመጣ በቴሲስ ከፍተኛ ውጤት ያመጣ ሲሆን በሞዴልነት የተመረጡ ስስት ተማሪዎችም ተሸልመዋል፡፡

በስተመጨረሻ የመሰናዶው ማሳረጊያ ነበር ፕሬዘዳንቱ የስንብት ንግግራቸውን የተማሪዎችን የትምህርት ተነሳሽነት መጀመሪያ እንጅ መደምደሚያ ወይም መቋጫ እንደይደለ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

መቐለ ዩኒቨርሲቲ
ህግ ት/ቤት
ተማሪዎች ማህበር

MULSSA VOICE

BY MEKELLE UNIVERSITY LAW SCHOOL STUDENTS ASSOCIATION

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች ድምፅ

“የሕግ ተማሪዎች ድምፅ” *(MULSSA VOICE) በ2009 ዓ.ም ጀምሮ በየ ሁለት ወሩ የሚታተም በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የሕግ ትምህርት ቤት መፅሔት ነው። መፅሔቱ ከማንኛውም ብሔር፣ ኃይማኖት እና የፖለቲካ ድርጅቶች አስተሳሰብ ጋር ያልወገነ የሕግ ተማሪዎች ነፃ ሓሳብን የሚያስተናብር ነው።*

Mail address
mikiasmelak@gmail.com
Phone number 0920 666 595

5Mail address
mikiasmelak@gmail.com
Phone number 0920 666 595

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች ድምፅ